

አላህ በሰጠህ ነገር ተብቃቃ

አንዴ ለዳዕዋ ወደ አንድ ሀገር ሄድኩ። ጠዋት ሁለት ትምህርቶችን ከሰጠሁ በኋላ ለዙሁር ሶላት አንድ ሰዓት ቀረ። እዚያ ሀገር ውስጥ ትልቅ የአዕምሮ ህመማን ሆስፒታል አለ። ሰዎች የእብዶች ሆስፒታል በማለት ይጠሩታል። በዚያ ሀገር ታዋቂ ዳኢ የሆነው አብዱል አዚዝ አብሮኝ አለ። መኪና ውስጥ ስንገባ "አብዱል አዚዝ ባለን ጥቂት ጊዜ አንድ መጎብኘት የምፈልገው ቦታ አለ" አልኩት። "የት መሄድ ፈለግክ? ጓደኛህ ሸህ አብደላህ የለም። ዶክተር አህመድም ደውዬለት ነበር ስልክ አያነሳም። ወደ ቅርሳ ቅርስ ሙዚየም መሄድ ፈለግክ ወይስ...?" አለኝ።

"የአዕምሮ ህመማን ሆስፒታልን ነው መጎብኘት የምፈልገው" አልኩት። "የእብዶችን?" ሲል በመገረም ጠየቀኝ።

"አዎ" አልኩት። ሳቀና "የአዕምሮህን ሁኔታ ለማጣራት ፈለግክ እንዴ?" ሲል ቀለደ። እኔም "አይደለም። ትምህርት ለመቅሰምና አላህ ለኛ የሰጠውን ፀጋ ለማስተንተን ፈልጌ ነው" አልኩት። አብዱል አዚዝ ስለ ሰዎቹ ሁኔታ ማሰብ ጀመረ። ትንሽ እንደተቆጣ ተረዳሁ። ምክንያቱም እሱ ሰሜታዊ ሰው ነው። በመኪናው ወደ ሆስፒታሉ ወሰደኝ። ዋሻ የሚመስል ቦታ ላይ ወረድን። ከሁሉም አቅጣጫ በዛፎች ተከቧል። በጣም የሚረብሽ አካባቢ ነው።

አንድ ዶክተር ጋ ሄድንና ሆስፒታሉን ያስጎበኘን ጀመር። ዶክተሩ የበሽተኞቹን ስቃይ ሲያወራ ስለ አንድ ነገር መስማትና ከቦታው ሄዶ ማየት ይለያያል አለ። ከተሰያዬ አቅጣጫ ድምፅ ይሰማል። ወደ አንድ ክፍል ስንገባ ከአስር በላይ ባዶ አልጋዎች አሉ። አንዱ ላይ አንድ ሰው ተኝቶ እጆቹንና እግሮቹን ያወናጭፋል።

"ምን ሆኖ ነው?" ስል ጠየቅኩት ለዶክተሩ።

"ይህ ሰው የአዕምሮ ህመምተኛ ነው። በየአምስትና ስድስት ሰዓቱ የሚጥል በሽታ ያፈራግጠዋል" አለ። ከአላህ በስተቀር ሀይልና ጉልበት ያለው የለም። "በሽታው ከጀመረው ስንት ጊዜ ሆነው?" አልኩት።

"ከአስር ዓመት በላይ ሆኖታል" አለኝ። ትልቅ ትምህርት አገኘሁና ፀጥ ብዬ መራመድ ጀመርኩ። ትንሽ ወደ ፊት ከተጓዝን በኋላ የተዘጋ ከፍል አገኘን። በሩ ላይ ትንሽዬ ቀዳዳ አለው። አንድ ሰው በቀዳዳው በኩል ወደ ውጭ እያየ ምን ለማለት እንደፈለገ የማይገባ ምልክት ያሳየናል። ወደ ውስጥ ለማየት ስሞክር ግድግዳውም መሬቱም ቡኒ ነው።

"ይህ ምንድን ነው?" ስል ጠየቅኩት ዶክተሩን። "የአዕምሮ ታማሚ ነው" አለኝ።

ከልቡ እንዳላዳመጠኝ ተረዳሁና "የአዕምሮ ታማሚ መሆኑን አውቄያለሁ። ባይታመም ኖሮ እዚህ አይመጣም ነበር። እኔ ታሪኩን ነው ማወቅ የፈለግኩት" አልኩት። እሱም "ይህ ሰው ግድግዳ ካዬ በእጆቹ፣ በእግሮቹና አንዳንዴም በጭንቅላቱ ግድግዳውን መደብደብ ይጀምራል። እጆቹና እግሮቹ ተሰባብረዋል። ጭንቅላቱ ተሰነጣጥቋል" አለኝ ዶክተሩ በሀዘን አንገቱን ደፋ አድርጎ። "አጠገባችን አድርገን ልንከባከበው ባለመቻላችን እዚህ ከፍል አስገብተን ቆለፍንበት" አለኝ። ግድግዳውም መሬቱም በአስፖንጅ ተሸፍኗል። እሱም የፈለገውን ያህል ይደበድባቸዋል። ዶክተሩ ወደፊት ይራመድ ጀመር። እኔና ጓደኛዬ እነዚህን ሰዎች ከገጠማቸው ችግር የጠበቅከን አላህ ምስጋና ይገባህ እያልን ተከተልነው። ትንሽ አለፍ እንዳልን አንድ አልጋ የሌለበት ከፍል ውስጥ ገባን። ከሰላሳ በላይ ሰዎች አሉበት። አንዱ አዘን ያደርጋል። አንዱ ይዘፍናል። ሌላው ይደንሳል። አንዱ ያለማቋረጥ ቤቱን ይዞራል። ከነሱ ውስጥ እግርና እጆቻቸው በሰንሰለት ታስረው የተቀመጡ ሶስት ሰዎች አሉ። ወዲያ ወዲህ ያማትራሉ። ለመንቀሳቀስ ይፈልጋሉ ግን አልቻሉም።

በጣም አዘንኩና ዶክተሩን ለምንድን ነው እነዚህን ሶስት ሰዎች በሰንሰለት ያሰራችኋቸው ስል ጠየቅኩት። የነዚህ ሰዎች ችግር ያገኙትን ሰው ሁሉ ይማታሉ። በር እና መስኮቶችን ይሰብራሉ። ለዚህም ከጠዋት ጀምሮ እስከማታ ድረስ እናስራቸዋለን አለኝ። ከመቼ ጀምሮ ነው እንደዚህ የሆኑት ስል ጠየቅኩት። አንዱ አስር ዓመቱ ነው። አንዱ ሰባት ዓመቱ ነው። አንዱ ደግሞ አምስት ዓመቱ ነው አለኝ። ስለሁኔታቸው እያስተነተንኩና ከዚህ የጠበቀኝን አላህ እያመሰገንኩ ከከፍሉ ወጣሁ።

"የሆስፒታሉ መውጫ በር ወዴት ነው?" ስል ጠየቅኩት። "አንድ ከፍል ይቀራችኋል። ምናልባት ከዚህ ከፍል በምታዩት ነገር ደግሞ ተጨማሪ ትምህርት ልታገኙ ትችላላችሁ ተከተሉኝ" አለን። እጇን ይዞ ወደ አንድ ትልቅ ከፍል ወሰደኝ። በሩን ከፈተውና ወደ ውስጥ ገባን። የሚታየው ትዕይንት ቀድሞ ከገባንበት ከፍል ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል። በርካታ ህመማን አሉ። አንዱ ይደንሳል። አንዱ ይዘፍናል...

። አንድ አስገራሚ ነገር አየሁ። አንድ ዕድሜው ከሃምሳ ዓመት በላይ የሚሆን ሰው ነው። ፀጉሩ ሸብቷል። መሬት ላይ ቁጢጥ ብሎ ተቀምጧል። አፍጥጦ ይመለከተን ጀመር። የፍርሃት ስሜት ይነበብበታል። ከዚህም በላይ እኔን በጣም ያስደነገጠኝና ዝለል ዝለል ያሰኘኝ ነገር ሰውዬው ራቁቱን መሆኑ ነው። ሀፍረተ ገላውን እንኳ መሸፈን የሚችል ቁራጭ ጨርቅ ላዩ ላይ የለም። በጣም ተረበሽኩ። አይኔ መቅላቱን የተመለከተው ዶክተሩ "ተረጋጋ። ይህ ሰው ልብስ ባለበሰነው ቁጥር በጥርሶቹ ያኝካቸዋል። ይቦጫጭቃቸዋል። ሊውጣቸውም ይሞክራል። በአንድ ቀን ከአስር በላይ ሙሉ ልብሶችን ልናለብሰው እንችላለን። ሁሉንም ቀዳዶ ይጥላቸዋል። ይህ ሰው አካሉ ላይ አንድ ነገር እንዲያርፍበት አይፈልግም። ስለዚህ በከረምትም በበጋም እንዲሁ ሆኖ ነው የሚቆየው። በዙሪያው ያሉ ሰዎች ሁሉ በአዕምሮ ህመም የተጠቁ በመሆናቸው የሱን ሁኔታ የሚያስተውሉ አይደሉም" አለኝ። ከፍሉን ለቅቄ ወጣሁ። ተጨማሪ ነገር ለማየት አቅም አልነበረኝም።

ለዶክተሩ "ባክህ እንውጣ" አልኩት። "የተወሰኑ ክፍሎች ይቀሩናል" አለ።

"እስካሁን ያየነው ነገር በቂ ይመስለኛል" አልኩት። ዶክተሩ መንገድ ጀመረ። ተከተልኩት። በድንገት የሆነ ነገር ትዝ እንዳለው ዓይነት ወደኔ ዞር አለና "ውድ ሽህ አንድ ታዋቂ ነጋዴ የነበረ ሰው እዚህ ውስጥ አለ። ሚሊዬነር ነው። አዕምሮውን ታመመ። ልጆቹ እዚህ አምጥተው አስገቡት። ሁለት ዓመት ሆነው። አንድ ኢንጂነርም አለ...።" በማለት ከተከበሩ በኋላ ስለተዋረዱ፣ ሀብታም ከሆኑ በኋላ ስለደኸዩ ሰዎች ይነግረን ጀመር። በሀሙማን ክፍሎች መካከል ስራመድ "ለባሪያዎቹ ሲሳይ ለሚሰጠው ጌታ ምስጋና ይገባው። ለፈለገው ይሰጣል። ለፈለገው ይነሳል" የሚለውን እያሰብኩ ነበር።

አላህ ለአንድ ሰው የተትረፈረፈ ሀብትና ጥሩ ጭንቅላት ይሰጠውና ጤና ይነሳዋል። ለሃያና ለሰላሳ ዓመት አልጋ ላይ ሊቆይ ይችላል። ሀብቱና ጭንቅላቱ ዋጋ ቢስ ይሆናሉ። ለሌሎቹ ደግሞ ጤና፣ ጥንካሬና ጥሩ ጭንቅላት ይሰጣቸውና ሀብት ይነፍጋቸዋል። በገቢያ ቦታ ዕቃዎቻቸውን በተከሻቸው ተሸክመው ታያቸዋለህ። ብዙ ለፍተው የሚያገኙት ገንዘብ ረሃባቸውን ለማስታገስ አያስችላቸውም። በዚህ መልኩ ነው አላህ አንዳንድ ነገሮችን ለሰዎች የሚሰጠውና አንዳንድ

ነገሮችን የሚከለክለው። የፈለገውንና የመረጠውን ይሰራል። ሰዎች በዚህ ላይ ምንም ዓይነት ምርጫ የላቸውም።

ስለዚህ ችግር የገጠመው ሰው የደረሱበትን ችግሮች ከመቁጠሩ በፊት አላህ የሰጠውን ሌሎች ፀጋዎች ማስታወስ ግድ ይለዋል። ሀብት ቢከለክልህ ጤና ይሰጥሃል። ሁለቱንም ከከለከለህ ጥሩ ጭንቅላት ይሰጥሃል። ሁሉንም ከከለከለህ ቢያንስ ቢያንስ ኢስላምን ሰቶሃል። እንኳን ደስ ያለህ በኢስላም ውስጥ በመኖርህና

በሱ ላይ በመሞትህ። ስለዚህ ድምጽህን ከፍ አድርገህ "አልሃምዱሊላህ" በል።

የነብዩ ባልደረቦች አላህ ስራቸውን ይወድድላቸውና እንዲህ ነበሩ። በዛት አል ሰላሲል ጦርነት ወቅት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አምር ኢብኑል አሰን የጦር መሪ አድርገው ላኩት። ሲደርስ ጠላት በቁጥር ብዙ መሆኑን ተረዳ። በመሆኑም ሀይል እንዲጨምሩለት የሚጠይቅ መልዕክት ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላከ። እሳቸውም አቡበከርንና ኡመርን ጨምሮ ሙሃጂሮችን በማሰባሰብ አቡ ኡበይዳ ኢብኑ ጀራህን መሪያቸው አድርገው ላኩ። ለአቡ ኡበይዳ "ሁላታችሁ መሊያየት የለባችሁም..." አሉት። አቡ ኡበይዳ ጦሩን ይዞ አምር ኢብነል አስ ዘንድ ደረሰ። አምርም "አንተ የመጣኸው የኔን ጦር ለማገዝ ነው። እኔ ያንተ ኮማንደር ነኝ" አለው።

"አይደለም። እኔም ደረጃዬን እይዛለሁ። አንተም ደረጃህን ያዝ" አለው አቡ ኡበይዳ። እኔም ላመጣሁት ጦር ኮማንደር ነኝ። አንተም ላመጣኸው ጦር ኮማንደር ነህ ማለቱ ነው።

"አይሆንም አንተ የመጣኸው እኔን ለማገዝ ነው" አለ አምር። አቡ ኡበይዳ ቅንና ደግ ሰው ነበር። ዓለማዊ ጉዳዮች ግድ የሚሰጡት ሰው አልነበረም። "አምር ሆይ! የአላህ መልዕክተኛ ሁላታችሁ መሊያየት የለባችሁም ብለውኛል። ስለዚህ አንተ ባትታዘዘኝም እኔ እታዘዝሃለሁ" አለው። አምር በምላሹ "ስለዚህ እኔ ያንተ ኮማንደር ነኝ። አንተ ደግሞ የኔ ኢንቮር ነህ" አለው። አቡ ኡበይዳ በዚህ በመስማማቱ አምር ኢብነል አስ ኢማም ሆኖ ሶላት አሰገደ። ከጦርነቱ በኋላ መዲና የገባ የመጀመሪያው ሰው አውፍ ኢብኑ ማሊክ (ረ.ዐ) ነበር። እንደደረሰ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ሄደ። "የሆነውን ነገር ንገረኝ" አሉት። ስለ ጦርነቱ ሁኔታና በአቡ ኡበይዳና በአምር መካከል የተፈጠረውን ነገር አጫወታቸው። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "የአላህ አዝነት በአቡ ኡበይዳ ኢብኑ ጀራህ ላይ ይውረድ" አሉ። በእርግጥም የአላህ እዝነት በአቡ ኡበይዳ ኢብኑ ጀራህ ላይ ይውረድ።

አንድ አስተሳሰብ

የህይወትህን መጥፎ ገፅታ ከመመልከትህ በፊት ብሩህ ገፅታውን ተመልከት። በአግጠኝነት ደስተኛ ትሆናለህ።



ተራራ ሁን

የዳዕዋ ስራ እንደጀመርኩ አካባቢ ነው። አንድ የዳዕዋ ስራን የሚቆጣጠር ሰው መጥቶ ወሰደኝ። መኪናው በጣም አሮጌ ናት። ስናወራ በቅርቡ ነው ያገባው። እዚያ አገር ላይ ባለው የመኸር ንረት ተማሯል። በዚህም ምክንያት አዲስ ወይም አሁን ካለው የተሻለ መኪና መግዛት እንዳልቻለ ነገረኝ። አላህ እንዲያግዘው ዱዓ አደረኩለት። ከዚያ መስጊድ ገባሁና ዳዕዋ አደረግኩ። መጨረሻ ላይ ጥያቄዎች ይቀርቡልኝ ጀመር። አንዱ ጥያቄ መኸር በዛብን ምን ይሻለናል የሚል ነበር። እኔም ደስ አለኝና "ይህ ጥሩ ጥያቄ ነው" አልኩ።

ከዚያም ስለ መኸር ንረትና በወጣት ወንዶችና ሴቶች ላይ ስለሚያሳድረው መጥፎ ተጽዕኖ አወራሁ። የአላህ መልዕክተኛ ሴት ልጆቻቸውን ከአምስት መዶ ዲርሃም በበለጠ የመኸር ገንዘብ ድረው እንደማያውቁ ተናገርኩ። ከዚያም "ይሄ ማለት የዚህ ጎሳ ልጆች ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጆች ይበልጣሉ ማለት ነው?" ስል ጠየቅኩ።

አንድ አዛውንት ተነሱና "ለምንድን ነው ስለ ልጆቻችን መጥፎ ነገር የምታወራው?" አሉ። ሌላውም ተነሳና "አዎ ልጆቻችንን እያጣጣልክ ነው" አለኝ። ሌላውም ተነስቶ...። አጣብቂኝ ውስጥ ገባሁ። ለዳዕዋ አዲስ ነኝ። በቅርብ ነው ከዩንቨርሲቲ ተመርቄ የወጣሁት። የመጀመሪያው ሰው ሲናገር ፈገግ አልኩ። ሁለተኛው ሰው ሲናገር ተመለከትኩትና ሳቅኩ። ለሶስተኛውም እንዲሁ። በመስጊዱ ጥግ ላይ የተቀመጡ አንዳንድ ወጣቶችም እየሳቁ ነበር። አንዳንዶቹ ምን እንደተፈጠረ ለማየት ከተቀመጡበት ተነሱ። ይህ ሰው ምን ፈረደበት የሚሉ ይመስላሉ። እኔም መልስ አለመስጠቴን ሲያዩ እነሱም ዝም አሉ። ከመካከላቸው አንዱ ተነሳና "ሰዎች ሆይ! ሸኹ ምን ለማለት እንደፈለገ እንዲያብራራ ፍቀዱለት" አላቸው። ሰውዬውን በጣም አመሰገንኩት። ከነልጆቻቸው ጭምር ይቅርታ ጠየቅኳቸውና ለማለት የፈለግኩትን ነገር ማብራራት ጀመርኩ።

ከሰዎች ጋር ስትግባባ የራስህን ስብዕና እየፈጠርክ ነው። በዚህ ግንዛቤያቸው መሰረት ካንተ ጋር እንዴት መሆን እንዳለባቸውና አንተን ማክበር ወይም አለማክበር እንዳለባቸው ይወስናሉ። አንድ ዛፍ ስሮቹ በደንብ ጠለቅ ያሉ ከሆኑ ንፋስ

አይገነድሰውም። ንፋሱ የቱንም ያህል ቢጠነክር። የአንድ ሰዓት ትዕግስት ድልን ያጎናፅፋል። አስተዋይ እየሆንክ በሄድክ ቁጥር ድከመትህ እየቀነሰ ይሄዳል። ብቃትህ እየጨመረ በሄደ ቁጥር ቁጣህ እየቀነሰ ይሄዳል። ምንም እንደማያንቀሳቅሰው ባህር። ነፋስ በጭራሽ እንደማያንቀጠቅጠው ተራራ ሁን።

በአንድ ስብሰባ ላይ፣ ወይም አንድ ሰው ቤት ወይም ቴሌቪዥን በመመልከት ላይ ሳለህ፣ ወይም ትምህርት ላይ አንድ ሰው ሊያበሳጭህ ቢሞክር ዝም በለው። አትናደድ ወይም አትገረም። ሰዎች በሰራው እሱን በመጥላት አንተን ያከብሩሃል። አቡ ሱፍያን ቢን ሀርብ ሸቀጡን ጭኖ ከቅፍለቱ ጋር ከሶሪያ ወደ መካ በመመለስ ላይ ነበር። ሙስሊሞች በመካ ቁረይሾች የተዘረፈባቸውን ንብረት ለማስመለስ ተንቀሳቀሱ። ሆኖም አቡ ሱፍያን ከነቅፍለቱ አመለጠና መልዕክት ልኮ ለቁረይሾች የተፈጠረውን ነገር ነገራቸው። ቁረይሾች በርካታ ሠራዊት ይዘው በመምጣት የበድር ጦርነት ተካሄደና ሙስሊሞች አሸነፉ። ከቁረይሾች ሰባ ሰዎች ሲገደሉ ሰባ ሰዎች ተማረኩ። ቀሪዎቹ በቁስለትና በረሃብ እየተሰቃዩ ተመለሱ።

አቡ ሱፍያን የተሸነፈውን የቁረይሽ ጦር ይዞ መካ ገባ። የመካ ህዝብ ከባድ ሀዘን ደረሰበት። አብዱላህ ቢን አቢ ረቢዓህ፣ ኢክሪማ ቢን አቢ ጀህልና ሰፍዋን ቢን አመያ አባቶቻቸው፣ ወንድሞቻቸውንና ልጆቻቸውን በበድር ጦርነት ካጡ ጥቂት ሰዎች ጋር በመሆን ወደ አቡ ሱፍያን ሄዱ። ከአቡ ሱፍያን ጋር የንግድ ሸርከና ላላቸው ሀብታሞች ሁሉ "ቁረይሾች ሆይ! በእርግጥም ሙሐመድ ከናንተ መካከል ትልልቅ ሰዎችን በመግደል ከፍተኛ ጉዳት አድርሶባችኋል። ስለዚህ በገንዘብ አግዙንና እንበቀለው" የሚል ጥሪ አቀረቡ። በዚህ ተስማሙ። አላህም ቁርዓን አወረደ።

"እነዚያ የካዱት ከአላህ መንገድ ሊከለከሉ ገንዘቦቻቸውን ያወጣሉ። በእርግጥም ያወጧታል። ከዚያም በነሱ ላይ ፀፀት ትሆንባቸዋለች። ከዚያም ይሸነፋሉ። እነዚያም የካዱት ወደ ገሃነም ይሰበሰባሉ።"

ከታማኞቻቸው ከቂናናህ ጎሳዎች፣ ከቲሃማ ህዝቦች፣ ከባሮችና ነፃ ሰዎች ጋር በመሆን መሳሪያዎቻቸውን ይዘው ቁረይሾች ተመሙ። ሴቶቻቸውንም ይዘው መጡ። ምንም እንኳ ወንዶቹ ከጦርነቱ የሸሹ ቢሆንም። አቡ ሱፍያን ከሚስቱ ከሂንድ ቢንት ኡትባ ጋር፣ ኢክሪማ ቢን አቢ ጀህል ከሚስቱ ኡሙ ሀኪም ቢንት አልሀሪዝ ጋር፣ አልሀሪዝ ከሚስቱ ከፋጡማ ቢንት አልወሊድ ቢን መጊራ ጋር በመሆን መጡ። የከሃዲያኑ ጦር መዲና አጠገብ ባለ ሸለቆ ጠርዝ ላይ ሰፈረ።

የአላህ መልዕክተኛ ይህን ሲሰሙ ባልደረቦቻቸውን ሰብስበው አማከሩ። "እዚሁ መዲና ውስጥ ሆነን እንጠብቃቸውና እዚህ ድረስ ከመጡ እዚሁ እንዋጋቸው ወይስ ምን ይሻላል?" በበድር ጦርነት ላይ ያልተሳተፉ ሰዎች በድር ላይ

የተሳተፉ ሰዎች ያገኙትን ደረጃ ለማግኘት በመመኘት "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ኡሁድ ድረስ እንሂድና እዚያው እንዋጋቸው" አሉ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ቤት ገቡና የጦር ልብሳቸውን ለብሰው ወጡ። ይህን ሲያዩ ሶሃቦች ነብዩ ለውጊያ ከመዲና እንዲወጡ አስገደድናቸው መሰል በማለት መፀፀት ጀመሩ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከፈለጉ መዲና ይቆዩ። ውሳኔው የርስዎ ነው መሆን ያለበት" አሏቸው። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "አንድ ነብይ ያጠለቀውን የጦር ልብስ አያወልቀውም። አላህ በሱና በጠላቶቹ መካከል ፍርድ ከመስጠቱ በፊት" አሉ።

አቡ ሱፍያን ኡሁድ ተራራ ስር ሲደርስ ሲያዩ በበድር ጦርነት ላይ ያልተሳተፉ ሙስሊሞች ተደሰቱ። "አላህ የምንመኘውን ነገር አመጣልን" አሉ። ነብዩም ለባልደረቦቻቸው "ወደ ጠላቶቻችን ለመድረስ አቋራጭ መንገድ የሚመራን ሰው ማን ነው?" በማለት ጠየቁ። የሀሪዛ ቢን አልሀሪዝ ጎሳ አባል የሆነ አቡ ኸይተማህ የሚባል ሰው "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እኔ እመራችኋለሁ" አላቸው። ሙስሊሞችን በሀሪሳህ ጎሳዎች መሬትና ጉብረት መካከል እየወሰዳቸው እያለ መርበአ ቢን ቀይዚ የሚባል ሰው እርሻ ላይ ደረሱ። መርበአ አይነ ስውር ሙናፊቅ ነው። ይህ ሰው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሙስሊሞች ጋር እያለፉ መሆኑን ሲያውቅ "አንተ የአላህ መልዕክተኛ ከሆንክ በእኔ እርሻ በኩል እንድታልፍ አልፈቅድልህም" እያለ አቧራ እያነሳ ላያቸው ላይ ይበትንባቸው ጀመር። ደካማው ሰው በእጁ ሙሉ አፈር ያዘና "ወላሂ ሌላ ሰው ሳልነካ አንተን ብቻ ለይቼ ባገኘሁህና ፊትህ ላይ በበትንኩብህ ጥሩ ነበር" ይላል። ሶሃቦች ይህን ሲሰሙ ተናደዱና ሊመቱት ወደሱ ተጠጉ። ሆኖም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "አትንኩት። እሱ እውር ነው - ልቡም አይኑም የታወረ" አሏቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መንገዳቸውን ቀጠሉ። ዘወር ብለው ሙናፊቁን አልተመለከቱትም። ምክንያቱም እሳቸው ብልህና አስተዋይ ሰው ናቸው። ሞኝ ሰዎችን ዘወር ብለው በመመልከት ጊዜ አያጠፉም። በመጥፎ ድርጊታቸውም አይበሳጩም።

እምነት...

ነፋስ ተራራን አያነቃንቅም። የሚጫወተው በአሸዋ ነው። እንደፈለገ ያደርገዋል። ያነሳዋል፤ ይጥለዋል።



መጠጥ በመጠጣቱ አትርገመው

በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ሁሉ የቱንም ያህል መጥፎ ቢሆኑ በውስጣቸው ጥሩ ነገር አለ። ሊያንስ ይችላል እንጂ። ያን ጥሩ ነገራቸውን ማጣጣም መቻል ድንቅ ነገር ነው። አንድ ወንጀለኛ አጥር በመዝለል ሰዎች ቤት ገብቶ ንብረት ዘርፎ በመውሰድ የተወሰነውን ጎዳና ላይ ላሉ ሰዎችና ለወላጅ አልባ ህፃናት ሊረዳ ይችላል። ለመስጊድ ግንባታም ሊለግስ ይችላል። አንዲት ሴት ዝሙት ሰርታ ያገኘችውን ገንዘብ የሚበሉት አጥተው በረሃብ የሚሰቃዩ ሰዎችን ልትመግብ ትችላለች። ወይም ሰው ለመግደል እየተጠባበቀ ሳለ የዚያን ሰው ልጅ ወይም ሚስት ሲያይ ልቡ ራርቶ የያዘውን ቢላዋ የሚጥል ሰው አለ። ስለዚህ ከሰዎች ጋር መቅረብ ያለብህ ከነሱ ላይ ባለው ጥሩ ነገር መሰረት መሆን አለበት - መጥፏቸውን ከማሰብህ በፊት።

ተወዳጁ ነብያችን (ሲ.ዐ.ወ) ለተሳሳቱ ሰዎች ይቅርታ በማድረግና ኃጥያት ውስጥ ስለ ወደቁ ሰዎች ጥሩ ነገር በማሰብ ይታወቃሉ። አንድ ኃጥያት የሚሰራ ሰው ሲያዩ በመጀመሪያ የኢማኑን ሁኔታ፣ ከዚያም የፍላጎቱንና የአመፁን ሁኔታ ይመለከታሉ። የእንቢተኝነቱን ደረጃ ያያሉ። ስለማንም ሰው መጥፎ አመለካከት የላቸውም። ሁሉንም እንደ ልጆቻቸውና እንደ ወንድሞቻቸው ነው የሚያዩት።

በነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ዘመን አንድ ሰው አስካሪ መጠጥ ይጠጣ ነበር። አንዴ ሰክሮ ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣ። እንዲገረፍ ተወሰነበት። ከጥቂት ቀናት በኋላ ቢድጋሚ ጠጥቶ ተያዘ። ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ዘንድ ሄዶ ተገረፈ። አሁንም ከጥቂት ቀናት በኋላ መጠጥ ሲጠጣ ተገኘና ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣ። ተገረፈና ለመሄድ ሲነሳ አንድ ሶሃባ "የአላህ እርግማን ይውረድብህ። ስንቴ ነው እየመጣ የሚገረፈው?" አለ። ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ፊታቸው ተቀያየረና "አትርገመው። ወላሂ አላህንና መልዕክተኛውን እንደሚወድ አውቃለሁ" አሉት። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከሰዎች ጋር ባለህ ግንኙነት ፍትኃዊ ሁን። ያላቸውን መልካም ነገር አስታውስ። መጥፏቸው ጥሩ ነገራቸውን እንዳላስረሳህ እንዲያስቡ አድርግ። ይህ ወዳንተ ያቀርባቸዋል።

ጥበብ...

በሌሎች ላይ የከፋትን ዛፍ ከመትከልህ በፊት የደግነትን ዛፍ ትከል። ከዚያም ውሃ አጠጣው።...